# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 36 ኛ ሳምንት
## ቤተ ክርስቲያን የሆነው የጣዖት ቤት

ዓላማ፡-

- ሰኔ 12 የቅዱስ ሚካኤልን በዓል የምናከብርበት ምክንያት መማር እና ስለ ዘመናዊ ጣዖት ማወቅና መጠበቅ

የሚጠና ጥቅስ፡

- *"ሌሎች አማልክት አይሁንላችሁ።"* ዘጸ. 20፣3

መግቢያ

- ሰኔ 12 የሚከበረው የቅዱስ ሚካኤል በዓል መከበር የጀመረው በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግብፅ ነበር።
- ክሊዮፓትራ በተባለች ንግሥት በተገነባ ቤተ ጣዖት ከዘመናት በፊት ሰኔ 12 የሚከበር በዓል ነበር።
- በዛሬው ትምህርታችንም ይህ ቤተ ጣዖት እንዴት እንደተሠራና ከዚያም እንዴት ወደ ቤተክስቲያንነት እንደተለወጠና የቅዱስ ሚካኤል በዓል ይከበርበት እንደጀመረ እንማራለን።

ትምህርቱ

- ንግሥት ክሊዮፓትራ በገነባችው ቤተ ጣዖት የእስክንድርያ ሰዎች ዙሐል የተባለ ጣዖት ያመልኩ ነበር። በየዓመቱም የእንስሳት መስዋዕት እያቀረቡ ያከብሩት ነበር።
- በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን እለእስክንድሮስ የተባለ ሊቀጳጳስ ተነስቶ እነዚህኑ ጣዖት አምላኪዎች ወንጌል ሰበካቸው ጣዖቱ ዙሐል የማይሠማ፣የማይናገር፤ምንም ማድረግ የማይችል በእነርሱ እጅ የተሠራ መሆኑን ነገራቸው።በነቢያትም የተነገረው ትንቢት በጌታችን መፈጸሙን ሠበከላቸው።
    - ከዚያም በሮማው ንጉስ በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመን እለእስክንድሮስ የኤሌክስአድርያ (ግብፅ) ፓትሪያርክ ሆኖ ተሾመ።
    - ከቆስጠንጢኖስ በፊት ያለው ዘመን የክርስትና የስደትና መከራ ዘመን ነበር።
    - *ክርስቶስ ለስሙ ሲመሰክሩ በስሙ ምን መከራ እንደሚያገኛቸው የነገራቸውን ታስታውሳላችሁ ?*
- ታላቁ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ግን ለክርስቶያኖች ነፃነትን አወጀላቸው።በዚሁ ዓመትም እለእስክንድሮስ ፓትርያርክ ሆኖ ተሾመ።
- እለ ስክንድሮስ ፓትሪያርክ ከሆነ በኋላም የዙሐልን ቤተ ጣዖት ቤተክስቲያን አድርጎ ቀደሰው የጣዖት ምስሎችንም አጠፋቸው።ጣዖት አምላኪዎችንም ክርስቲያን አደረጋቸው።
- ለጣዖት በመሠዋት ፋንታም እግዚአብሔርን እንደያመልኩና ድሆችን እንዲረዱ አደረገ። ቀኑም የቅዱስ ሚካኤል ቀን ሆኖ ተከበረ።ከዚያም በኋላ ሰኔ 12ትን ቅዱስ ሚካኤልን እያሰቡና ድሆችን እየረዱ እግዚአብሔርን የሚያከብሩበት በዓል ሆነ።

ከዚህ ታሪክ የምንማረው ጠቃሚ መልእክት

- ከታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በፊት ጣዖት አምልኮ በዓለም ላይ ተንሠራፍቶ ነበር።
- አሁንም እንደበፊቱም ባይሆን ጣዖት አምላኪዎች አሉ።ጥቅመኛነትና ግላዊነትም የዘመናችን ጣዖታት ናቸው።
- እለእስክንድሮስ የዙሐል ቤተ እምነትን ጣዖት አምልኮ በአምልኮተ እግዚአብሔር ቀይሮታል።

ማጠቃለያ፡-

- የታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመን የክርስትያኖችን መከራ አስቀርቶታል።ቤተ ጣዖቱም ተዘግቷል። ሰኔ 12 ቀን የምናከብረው ቤተ ክርስቲያን ጣዖተ አምልኮ ላይ ያገኘችውን ድል ነው።

የቆስጠንጢኖስ እናት ታስታውሳላችሁ? ለመምህር አስረዱ።

የልምምድ ጥያቄዎች

1. የዙሐል ቤተ ጣዖት ለምንና በማን ተገነባ?
2. የዙሐልን ቤተ ጣዖት ወደ ቤተክስቲያንነት የቀየረው ማነው? አምላኪዎችንስ ማን ክርስቲያን አደረጋቸው።
3. የክርስቲያኖችን ስደት ያስቆመው የሮም ንጉሥ ማነው?
4. የዘመናችን ጣዖት አምልኮ ምን ይመስላል?
5. የምታከብሩት ቅዱስ ማነው? ለምን?
6. መስቀሉን ያገኘችው ንግሥት እና የክርስቲያኖችን ስደት ባስቀረው ንጉሥ መሐል ያለው ግንኙነት ምንድነው? ስማቸውስ ማን ይባላል?

ይቆየን።